# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ




## ከኦገስት 1-31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከሴፕቴምበር 1-30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና

## ምክረ ሃሳብ


ሴፕቴምበር 2026

አዲስ አበባ

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፈዉ የኦገስት ወር በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ112 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1) ፡፡


በተጨማሪም በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 51-133 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል አዳዋ 60.5፣ አምባማሪያም 70.2፣ አሳሳ 60፣ አየዉ 65፣ ቡለን 65፣ ደብረ ታቦር 63.4፣ ዳንግላ 74፣ ደብረ ሲና 63.5፣ ጊምቢ 82.4፣ ሂርና 98.3፣ ሊሙገነት 61.7፣ ማይጨዉ 79.5፣ ማሻ 133፣ መተማ 61.7፣ ነቀምት 89.4፣ ሰመራ 60.2፣ ወረኢሉ 78 ይገኙበታል ፡፡





ምስል1: ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፈዉ የኦገስት ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታና ጎፋ፣ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ101-450 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


በኦገስት ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ አርሲ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታና ጎፋ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ የተቀራረበ እና በጥቂት የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነው የኦገስት ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ለግብርናው የስራ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተለይም በማደግ፣ በማበብና ፍሬ በማፍራት ላይ ባሉ የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦት በተሻለ ሁኔታ እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበር፡፡ በአንፃሩ በሶስተኛዉ አስር ቀናት አልፎ አልፎ በዋግህመራ ዞን ከነበረው በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በሰብሎች ላይ ጉዳት አድረሷል፡፡ እንዲሁም በሁለተኛዉ አስር ቀናት ከመኸሩ ዝናብ መቆራረጥ ጋር ተያይዞ በደሴ ዙሪያ ወረዳ 012 እና 041 ቀበሌዎች የፌንጣ ክስተት የተስተዋለ ሲሆን ተባዩ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ አርሶ አደሮች ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት አፋጣኝ የመከላከል እርምጃ በመውሰድ መከላከል ተችሏል (ካርታ 4)።

## 1.4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳልፈነው የኦገስት ወር በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ አባይ፣ በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ተከዜ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ አይሻ፣ አፋር ደናክል፣ እንዲሁም የኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በተፋሰሶችና ንዑስ ተፋሰሶች ውስጥ ያለውን የውሃ ክምችት በማሻሻል ወደ ግድቦችኛ የውሃ መያዣዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከመጨመር አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

Ethiopian Meteorology Institute

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2. መግቢያ


በመደበኛ ሁኔታ ሴፕቴምበር የክረምት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ ከሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆነው የሰነበቱት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ማግኘት ይጀምራሉ። በዚህም መሠረት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም ከ12-23 ለሚደርሱት ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ከ3-15 ቀናት ያህል ከ20-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። የደቡብና የደቡብ ምስራቅ ስፍራዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የሚጨምር በመሆኑ 30-100 ሚ.ሜ ከ3-12 ቀናት ይደርሳል፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ


በመደበኛው ሁኔታ የክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች የፀሐይ አቅጣጫን ተከትለው ከሴፕቴምበር የመጀመሪያው ሳምንት በኋላ ከሰሜንና ሰሜን ምሥራቅ አካባቢዎች የሚዳከሙ ሲሆን በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና መካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ስርጭት ይኖራቸዋል፡፡ በወሩ መጨረሻ ሳምንት ደግሞ ዝናብ ሰጪ ክስተቶቹ እየተዳከሙ በመምጣት ከአብዛኛዎቹ የሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛውና ምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች በበጋው ደረቅ የአየር ጠባይ ተፅዕኖ ስር መሆን ይጀምራሉ።

በመጪው ሴፕቴምበር በምዕራብ አማራ፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የኦሮሚያ ምዕራባዊ አጋማሽ ላይ የክረምቱ ዝናብ እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ የሚቀጥል ሲሆን፤ በመጠን ረገድ ደግሞ አብዛኛው የምዕራብ ትግራይ፤ የአማራ ምሥራቃዊ አጋማሽ፤ የመካከለኛው ኦሮሚያ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት አካባቢዎችን ጨምሮ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ እና በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ ከመደበኛው በታች ዝናብ እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ በተለይ እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም የምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች፣ የሶማሌ ማዕከላዊ እና ደቡባዊ ክፍል፣ ከኦሮሚያ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ እንዲሁም ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ የሲዳማ እንዲሁም የአፋር ደቡባዊው ክፍል ቀላል መጥን ያለዉ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል (ካርታ 6 እና 7)። በሌላ በኩል ደግሞ የክረምት ዝናብ ሰጪ ክስተቶች ወደ ደቡብ በሚያደርጉት

እንቅስቃሴ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ ከደቡብ ኦሮሚያ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፣ የደቡብ ሶማሌ አካባቢም ከወሩ አጋማሽ ጀምሮ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.2 እ.አ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የመስከረም ወር በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው የእርጥበት ለግብርናው ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ እንዲሁም ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች፣ ለፍራፍሬ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች የሚያስፈልጋቸውን የእርጥበት መጠን ከማሟላት አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ነዉ፡፡ በአንፃሩም የእርጥበት ሁኔታው ባለፉት የክረምት ወራት በመደበኛ ሁኔታ ደረቅ ሆነው በሰነበቱትና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ወደ ሆኑት ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች የሚኖረው መስፋፋት የማሳ ዝግጅት ለማድረግና የበጋ ወቅት ሰብሎችን ለመዝራት እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በሌላ በኩል በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ ዝናብ ሊኖር ስለሚችል ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት፣ የአረም መስፋፋት፣ በየጣልቃው ከሚኖረው

Ethiopian Meteorology Institute

ሙቀት ጋር ተዳምሮ ፀረ ሰብል ተባይ ክስተት ሊኖር ስለሚችል አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ተገቢዉን ጥንቃቄ ማድረግ ያሰፈልጋል። በተጨማሪም ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን እርጥበት በማሰባሰብና በማከማቸት በደረቅ ሰሞናት ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

## 2.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጭው የሴፕቴምበር ወር በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ላይኛውና መካከለኛው አባይ፣ የታችኛው ተከዜ፣ ላይኛውና መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ እንዲሁም የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና በጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ የገጸ-ምድር የውሃ ፍሰትን የሚያሻሽል ሲሆን፤ በተጨማሪም የከርሰ ምድር የውሃ ሃብት ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ  የከተማም ሆነ ገጠራማ አካባቢዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ፣ የወንዞች ሙላትና ሊኖረው ይችላል። ስለሆነም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የወንዝ ዳርቻዎች፣ በረግረጋማ እንዲሁም ረባዳማ እና ተዳፋት በሆኑ አካባቢ በሚኖሩ የማህበረሰቦች ክፍሎች በህይወትና በንብረትና እንዲሁም በመሰረተ ልማት ላይ ጎዳት እንዳያደርስ አስፈላጊው የቅድመ ጥንቃቄና ቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ በኦጋዴንና በታችኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም በመካከለኛውና ታችኛው አዋሽ፣ በታችኛው ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ቀላል የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራችው ይጠበቃል።